# ያረጁ ስምምነቶችን አፈራ አራግፎ የመጠቀም ፖለቲካ

ሙዘይን አብደላ 01/29/14

ብዙ ጎረቤት አላት፡፡ የንክኪዋ መጠንም ሆነ ፈርጅ እንዲሁ የተበራከተ ነው፡፡ በእርግጥ የጎረቤትም ሆነ የጉርብትና ችግር የለባትም፡፡ በአጎራባች ሀገራት ተከባለችና–ኢትዮጵያ፡፡ ኤርትራ፣ ጅቡቲ፣ ሱዳን፣ ሶማሊያ እና ኬንያ አጎራባቿ ናቸው፡፡ ከሀገራቱ ጋር በየብስ ትዋሰናለች፡፡ የንክኪ መጠኗም በጋራ ጥቅም ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ጉርብትናው በሠላሙ ወቅት ጥቅሙ የሚያመረቃ፣ ቋቱም በስንቅ የተሞላ ይሆናል፡፡ በአንጻሩ ችግር ካለ ጉዳቱ የከፋና የጎረበጠ ብሎም የእያንዳንዱን ሀገር ህልውና ለጥፋት የሚፈታተን እንደሚሆን እርግጥ ነው፡፡

ኢትዮጵያ ከአጎራባቾቿ ጋር በጋራ ጥቅም ላይ የተመሠረተ ግንኙነት እንዲኖራት ሁሉንም ሀገራት ተጠቃሚ የሚያደርግ ፖሊሲ ትከተላለች፡፡ ይሁንና ሠላም የሚገኘው በሁሉም ወገን ተፈላጊ ሲሆን ብቻ ነው፡፡ በአንድ ወገን ስለተፈለገ ብቻ የሚገኝ ነገር አይደለም–ሠላም፡፡ ጦር ናፋቂ አንዳንድ አጎራባች ሀገሮች የሚከተሉት ቀጣናውን የማመስ ርዕዮትና ፍልስፍና ለአካባቢው የፀጥታ መታወክ ሥጋት መሆናቸው አልቀረም፡፡ ይህ ሲባል የፀጥታ ሥጋትነታቸው በየብስ ከሚያዋስናቸው ብቻ ላይሆን ይችላል፡፡ ከዚያም እልፍ ሲል ባህር አቋርጠው የአየር ንክኪ አለን ከሚሉት ጋርም ሲያላትማቸው ይስተዋላሉ፡፡

ለኢትዮጵያ ታላቁ የአባይ ወንዝ ዋነኛው የንክኪ ዘርፍ ነው፡፡ ከአንዳንዶች ጋር በሚኖራት ግንኙነት ላይ የራሱ አንድምታ አለው፡፡ የወንዝ ንክኪ ከሌሎች አቀራኝ ክስተቶች በጎላ መልኩ በሀገራት ግንኙነት ላይ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ተጽዕኖ እንደሚኖረው ይታመናል፡፡ የወንዝ ንክኪ እንደ የብስ ንክኪ ፍንትው ብሎ የሚታይ ቀጥተኛ አይሁን እንጂ ከጠቀሜታውም ሆነ ከጉዳቱ አንጻር ሲቃኝ ከፍተኛ ነው፡፡

የዚህ ጽሁፍ ትኩረት አባይ ወንዝ ነውና ወደዚያው እናምራ፡፡ ኢትዮጵያ ከግብጽ ጋር ያላት ንክኪ እንደ የብስ ንክኪ ቀጥተኛ አይደለም፡፡ ይሁንና በሁለቱ ሀገራት መካከል ያለው ግንኙነት ውስብስብና ከሁሉም የላቀ ሆኖ ቆይቷል፡፡ በተለይም ወታደራዊ ኃይላቸው የፈረጠመ፣ ፖለቲካዊ ክንዳቸው የረዘመ፣ ምጣኔ ሀብታቸው የደለበ ሀገሮች ጥቅማቸውን ለማስከበር አልፎ ተርፎም ተጽዕኗቸውን ለማሳረፍና አመለካከታቸውን ለማስረፅ ከታላሚ ሀገሮች ጋር የየብስ ንክኪ ያላቸው ሀገሮችን መገልገያ ማድረጋቸው

አይቀርም፡፡ በአጎራባች ሀገሮች አማካይነት የሚከናወነው ወታደራዊና ዲፕሎማሲያዊ ትግልም የዚህ መሰሉ ንክኪ ውስብስብና የእጅ አዙር ተፅዕኖ አንዱ መገለጫ ነው፡፡

ኢትዮጵያ በአባይ ውኃ አማካይነት በተለይ ከግብጽ ጋር ያላትን ንክኪ ከተመለከትን ከዚህ ዓይነት ግንኙነት እምብዛም የራቀ አለመሆኑን ለመረዳት አስቸጋሪ አይደለም፡፡ በተለይም ቀደምቶቹ የግብጽ መሪዎች ከኢትዮጵያ ጋር በተለያየ መንገድ ንክኪ ባላቸው ሀገሮች በመጠቀም ኢትዮጵያ ውስጥ ያላቸውን ጥቅም ለማስከበር ደፋ ቀና ሲሉ ረዥም ዓመታትን አሳልፈዋል፡፡ በአንጻሩ ኢትዮጵያ ለመልካም ጉርብትና ከምንም በላይ ቅድሚያ በመስጠት የአጎራባች ሀገሮች ሠላምና ደህንነት እንዲጠበቅ አልፎ ተርፎም ለአፍሪካ አንድነት፣ ነጻነትና ብልጽግና ወሣኝ ሚና ለመጫወቷ ታሪክ ዛሬም ድረስ የሚያነሳው ህያው ምስክር ነው፡፡

አብነት እንጥቀስ፡፡ የቀድሞው የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የአሁኑ የአፍሪካ ህብረት እንዲመሠረት ኢትዮጵያ ያበረከተችው ግንባር ቀደም ተሳትፎ ዋንኛው ነው፡፡ አጎራባቿ የሆኑት ሱዳንና ሶማሊያ የውስጥ ችግሮቻቸውን እንዲፈቱ የተጫወተችው ሚናም ትልቅ ሥፍራ የሚሰጠው ነው፡፡ በአህጉር ደረጃ የኮንጎ፣ የላይቤሪያ፣ የሩዋንዳና የቡሩንዲን የውስጥ ግጭቶች ለማስወገድ ያደረገችው ጥረትና አሁን በሱዳን ዳርፉር እና በሶማሊያ እያካሄደች ያለችው የሠላም ማስከበር ተልዕኮ በሁሉም የሠላም ወዳድ ማኅበረሰብ ዘንድ እያስመሰገናት ያለ መልካም ተግባር ነው፡፡

ይህ ብቻ አይደለም፡፡ ለዚምባቡዌና ለደቡብ አፍሪካ ነጻነት ያደረገችው አስተዋጽኦ በማንም የሚዘነጋ አይደለም፡፡ ይሁንና ይህ ቅንና በጎ እንቅስቃሴ በአንዳንድ የኢትዮጵያ አጎራባቾች በኩል አዎንታዊ ምላሽ አላስገኘም። ይልቁንም አንዳንዶቹ የኢትዮጵያን ሠላምና ዕድገት ከማይመኙ ኃይሎች ጋር በማበር የሀገሪቱን ሉዓላዊነት ሲፈታተኑ የቆዩባቸውን አጋጣሚዎች እንቁጠር ከተባለ ጥቂት የሚባል አይደለም፡፡

እንደ እውነቱ ከሆነ እነዚህ አጎራባች ሀገሮች ይህን አሉታዊ እንቅስቃሴ የሚያደርጉት ከብሔራዊ ጥቅማቸው አኳያ ጠቃሚ ሆኖ ስላገኙት ብቻ አይደለም፡፡ በአካባቢው ሠላም ከሰፈነ የውስጥ ችግራቸው ገንፍሎ ስለሚወጣና በሥልጣን ላይ የመቆየት ህልውናቸውም ስለሚያከትም በተቻላቸው አቅም የህዝባቸውን ቀልብ ለመለወጥ የሚያደርጉት ጥረት ጭምር ነው፡፡

እነዚህ መንግሥታት ከዘለቄታዊ ብሔራዊ ህልውናቸው ይልቅ ጠባብ ቡድናዊና ጊዜያዊ ጥቅምን በማስቀደም የተሳሳተ የፖለቲካ ስሌት በመከተል አጎራባቾቻቸውን በመተንኮስ ተግባር ላይ ሲጠመዱ ይስተዋላሉ፡፡ የኢትዮጵያና ግብፅን ታሪካዊ ግንኙነት እንመልከት፡፡ የሁለቱ ሀገራት ህዝቦች ከአንድ ወንዝ ውኃ የሚጠጡ፣ የረዥም ጊዜ የታሪክ ትስስር ያላቸው፣ በዘመናዊ ታሪካቸውም የአፍሪካ አንድነት ድርጅት መሥራቾች መሆናቸው እውነት ነው፡፡ ሆኖም እንደቆየው ትስሰራቸው ግንኙነታቸው በሚፈለገው መልኩ ጠንካራ ነበር ብሎ ለማለት አያስደፍርም፡፡

በተለይም ግብጽ ባለፉት መንግሥታቶቿ ናይልን በተመለከተ ስታራምድ የቆየቻቸው ፖሊሲዎች በዓይነት የተለያዩ ቢመስሉም በይዘት ተመሣሣይ ስትራቴጂ፣ ግባቸውም ቢሆን አንድና አንድ ነው – "ዓባይን ከምንጩ" የሚል፡፡ እዚህ ላይ ያለፉት የግብጽ መንግሥታት በአባይ ወንዝ ላይ ሲያራምዱ የቆዩትን ፖሊሲዎች ፈርጅ በፈርጅ ከፋፍሎ ማየት ጠቃሚ ይሆናል፡፡ የአባይ ውኃ ጉዳይ  ከትናንት የዘለቀ ዘመን ያስቆጠረ፣ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስም ዘለቄታዊ እልባት ያላገኘና ሥር የሰደደ ጥያቄ ነው፡፡

በኢትዮጵያ ላይ ቀና አመለካከት ያልነበራቸው የግብጽ ባለሥልጣናትና ምሁራን ኢትዮጵያ የተረጋጋች ከሆነች መሪዎቻቸው የመንፈስ እርጋታ፣ ህዝቡም ሠላምና እፎይታ እንደማያገኝ ሲሰብኩ ኖረዋል፡፡ እነዚህ የግብጽ ልሂቃን የሀገራቸው መንግሥት ፖለቲካዊ መረጋጋት፣ የዜጎቻቸውም ምጣኔ ሀብታዊ ብልጽግናና የህዝቡ ውሎ ማደርም ዋስትና የሚኖረው "አባይን ከምንጩ መቆጣጠር ሲቻል ነው" የሚል አስተሳሰብን ሲያቀነቅኑ ቆይተዋል፡፡ ይህም በኢትዮጵያ ላይ ለነበራቸው አፍራሽ አመለካከት መንስዔው የተሳሳተ እምነታቸው ነው ብሎ መደምደም ይቻላል፡፡

አባይን ከምንጩ መቆጣጠር የሚለው መርህ ግብጾች በራሳቸው የፈጠሩት ሳይሆን ከቅኝ ገዥዎቻቸው እንግሊዝ የቀሰሙት ትምህርት ነው፡፡ በተለይም በ18ኛ ክፍለ ዘመን እ.ኤ.አ ከ1861 እስከ 1949 የኖረው እውቁ እንግሊዛዊ የፖለቲካ ጂኦግራፊ ምሁር ጆን ማኪንደር "The heart land" (the land foyer of Eurasia)" የሚባለውን አካባቢ ብሎም ዓለምን ለመቆጣጠር ያስችላል የሚለውን አውደ ሀሳብ ሲያቀነቅንና ሲያራመድ ቆይቷል፡፡

በእንግሊዝ የቅኝ አገዛዝ ፖሊሲ ላይ የጎላ ተጽዕኖ የፈጠረው ይህ አስተሳሰብ በግብጽ መሪዎችም ዘንድ ሰርጾ በመግባቱ የመምህራቸውን የማኪንደርን ፈለግ በመከተል "የራስጌ

ተፋሳሽ ሀገሮችን መቆጣጠር ዓለምን መቆጣጠር ያስችላል" በሚል የተስፋፊነት እሳቤ በመመራት የአባይን ሸለቆ በተለይም ኢትዮጵያን ለመቆጣጠር ያልቧጠጡት ደመና፣ ያልዘገኑት ጉም አልነበራቸውም፡፡ በቱርክ ሥልጣን የግብጽ አስተዳዳሪ ሆኖ የተሰየመው መሐመድ አሊ ፓሻ በግብጽ ያለውን የማምሉክ አስተዳደር ካስወገደ በኋላ ጠንካራ ማዕከላዊ መንግሥት በማቋቋም በርካታ ግድቦች፣ እርከኖችና ሰፋፊ የመስኖ ሥራዎችን ጀመረ፡፡

ዘመናዊ የጦር ሠራዊት በማደራጀትም ወደ ሱዳን፣ ኡጋንዳና ኢትዮጵያ ወሰን ያደረገው የተስፋፊነት እንቅስቃሴ በታሪክ አጥኚዎች እይታ ይህን የግብጽ መሪዎች ፍላጎት በማሳየት ረገድ የጎላ ድርሻ ይሰጠዋል፡፡ በዚህም ብቻ አላበቃም። እስማኤል ፓሻ የተባለው የመሐመድ አሊ ፓሻ የልጅ ልጅ የአያቱን ህልም እውን ለማድረግ በመጀመሪያ ሶማሊያንና ሐረርን ለመቆጣጠር በመቀጠል በ1875 በጉራዕ፣ በዓመቱ በ1876 ደግሞ በጉንደት ያደረጋቸው የጦርነት እንቅስቃሴዎች ለአብነት የሚነሱ የጠብ አጫሪነት እርምጃዎች ተጠቃሾች ናቸው፡፡

እዚህ ላይ በግልጽ ማየት የሚቻለው ቁም ነገር በተለያዩ ጊዜያት የግብጽ መሪዎች ዘመናዊ የጦር ሠራዊት አዳራጅተው የተሰፋፊነት እንቅስቃሴ ማድረጋቸውን፣ ይበጀናል ያሏቸውን የጠብ አጫሪነት ርምጃዎች መውሰዳቸውን ነው፡፡ በቀደምት የግብጽ ፖለቲካዊ ህይወት ውስጥ ከመሐመድ አሊ ፓሻ እስከ ንጉስ ፋሩቅ ድረስ በትረ መንግሥቱን እያፈራረቁ የጨበጡ የግብጽ መሪዎች በሙሉ ታላቁ ህልማቸው ያንኑ አባይን ከምንጩ መቆጣጠር የሚለውን ዕቅድ ነበር፡፡ በመጀመሪያው የግብጽ ፖሊሲ ጎራ የሚካተት ቁልፍ ተግባራቸውም ይኸው ነበር፡፡

ይሁንና የጉራዕና የጉደት የፀረ ወረራ አሻራ፣ የአድዋው ፀረ ቅኝ አገዛዝ ድል "አባይን ከምንጩ መቆጣጠር" የሚለውን የግብጽ ህልም ወደ እውንነት ሊለወጥ የማይችል መሆኑን በግልጽ ጠቆመ፡፡ ኢትዮጵያውያን ለሉዓላዊነታቸውና ለነጻነታቸው ያላቸውን ጽኑ ዓላማ የሚያመላክቱ ሆነ፡፡ በመሆኑም የግብጽ ኢትዮጵያን የማጠቃለል ፖሊሲ ፋይዳ ትርጉም የለሽ እንቅስቃሴ እንደሆነ በማያሻማ ሁኔታ አሳየ፡፡

ስለሆነም የግብጽ መራሂ መንግሥታት ኢትዮጵያን የማጠቃለል ፖሊሲ ገቢራዊ ሊሆን እንደማይችል ተገነዘቡ፡፡ ስለሆነም ስትራቴጂያዊ ዓላማው ያው ሆኖ በታክቲክ ደረጃ ለየት

ያለ ፖሊሲ መከተል ግድ ሆነባቸው፡፡ በዚህም መሠረት የኢትዮጵያን ሁኔታ በቅርበት በመከታተል የውስጥ ጥቃቅን ሁኔታዎችን በማጋጋል፣ አኩራፊ ኃይሎችን በማደራጀት፣ በመርዳትና በመንከባከብ አልፎ ተርፎም በቀጥታ በማስፈራራትና ወታደራዊ ኃይል በመገንባት ኢትዮጵያን የማዳከም እንቅስቃሴ ማራመድን ምርጫቸው አድርገው ያዙ፡፡

ማንኛውም ዓይነት ርትዓዊና ፍትሃዊ የውኃ አጠቃቀም ጥያቄ የግብጽን ብሔራዊ ህልውና ለድርድር የሚያቀርብ ጭብጥ አስመስለው የተውገረገረ ትርጉም ለመስጠት የማያቅማሙ የሃያኛው ክፍለ ዘመን አስተሳሰብ አራማጆች በግብጽ የፖለቲካ እልፍኝ ውስጥ ውርውር ማለታቸው ግን አልቀረም፡፡ "አባይ የለም ማለት ግብጽ የለችም" የሚለው ጽንፈኛ ያረጀና ያፈጀ አስተሳሰብ አንግበው የውኃ አጠቃቀም ጭብጦችን በደምሳሳው የሚያዋድቁትን ያህል ብቻ ሳይሆን "ኢትዮጵያ አለች ማለት የግብጽ ህዝብ በልቶ አያድርም" የሚል ሥር የሰደደ ኋላ ቀር፣ የተዛባና ያደፈ አመለካከት የሚያቀነቅኑ የተወሰኑ ልሂቃን ኢትዮጵያን ለማሽመድመድ ወይም ለእነርሱ ዓላማ ስኬታማነት እንድትንበረከክ ለማድረግ የማይፈነቅሉት ድንጋይ አልነበረም - ምንም እንኳን ባይሳካላቸውም፡፡

እ.ኤ.አ ከ1952ቱ የግብጽ አብዮት ወዲህ ፕሬዚዳንት ጋማል አብዱልናስር ከንጉስ አፄ ኃይለ ሥላሴ ጋር የቅርብ ግንኙነት ስለነበራቸው ግብጽ በኢትዮጵያ ላይ ዓይኑን ያፈጠጠ የከፋ እንቅስቃሴ አታደርግም ተብሎ ይታሰብ ነበር፡፡ ሆኖም ከ1956 የስዊዝ ካናል ጦርነት ወዲህ "የውኃ ደህንነትን ማስጠበቅ" በሚል ግብጽ ኢትዮጵያን በማግለል ያደረገችው የአስዋንን ግድብ የመገንባት እንቅስቃሴና የአባይን ውኃ ከሱዳን ጋር ብቸኛ ተጠቃሚ ለመሆን ያኔ ያደረጉት የ1956ቱ የተናጠል ስምምነት ሲታይ ግብጽም ሆነች ተባባሪዋ ሱዳን ያኔ በኢትዮጵያ ላይ ቀና አመለካከት ነበራቸው ለማለት አያስደፍርም፡፡

ፕሬዚዳንት አንዋር ሣዳት በትረ መንግሥቱን ከጨበጡ በኋላም ቢሆን በህቡዕ የነበረውን ኢትዮጵያን የማጥቃት እንቅስቃሴ በገሃድ በማውጣት የለየለት የጠብ አጫሪነት ፖሊሲ ማራመድ ጀመሩ፡፡ በወቅቱ የሀገሪቱ የመከላከያ ሚኒስትር የነበሩት ሌተና ጄኔራል ከማል ሐሰን አሊ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ "ግብጽ ሥልታዊ ጠቀሜታን ለማስከበር ወደ ጦርነት ታመራለች" ማለታቸውን ማስታወሱ ተገቢ ይሆናል፡፡ የግብፅ የመስኖ ሚኒስትር አብዱልአዚም አብዱል አታበሜይ በበኩላቸው "ኢትዮጵያ የአባይን ውኃ እንድትጠቀም ግብጽ በፍፁም አትፈቅድም" ሲሉም ተደምጠዋል፡፡ ፕሬዚዳንት አንዋር ሣዳት በፊናቸው

“ኢትዮጵያ በጣና ሐይቅ ላይ ግድብ ለመስራት ብትሞክር ግብጽ ጦርነት ታውጃለች” በሚለው ንግግራቸው ያንፀባረቁት የሀገራቸውን ተንኳሽ ፖሊሲን ነበር፡፡

ከዚህም ባሻገር ግብጽ የተለያዩ ፀረ ኢትዮጵያ ኃይሎችን ከማደራጀትና ከማስታጠቅ በተጨማሪ የጣና በለስ ፕሮጀክት ስኬታማ እንዳይሆን የዓለም ባንክና የዓለም አቀፉ የገንዘብ ድርጅት ለኢትዮጵያ የውኃ ልማት ብድር እንዳይሰጡ ያደረገችው ህቡዕ እንቅስቃሴ የሚረሳ አይደለም፡፡ በዘመነ ሆስኒ ሙባረክ የግብጽ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አሚር ሙሣ በአንድ ወቅት “ኢትዮጵያ መብታችንን እስካልነካች ድረስ ዕቅዶቿን ለማሰናከል ፍላጎት የለንም” ማለታቸው የቅርብ ጊዜው ትውስታ ነው፡፡

ይህ በገጽታው ምክንያታዊ የሚመስለው ሆኖም በሚኒስትሩ አማካይነት የተንፀባረቀው ይፋዊ አቋም በለሆሳስ የቀረበ ዛቻ መሆኑ ከማንም የተሰወረ አልነበረም፡፡ ምክንያቱም “መብታችንን እስካልነካች ድረስ” ከሚለው ሐረግ፣ ግብጽ ከኢትዮጵያ በየዓመቱ የምታገኘው 84 ቢሊዮን ኪዮቢክ ሜትር ውኃና ከሙቶ ሺህ ቶን በላይ ለም አፈር “ቅንጣት ቢጎድል ወዮላችሁ” የሚል የማስጠንቀቂያ ደወል መሆኑ ለማንም አይጠፋውም፡፡ ሌላኛው ወጥመዳዊ ሥልት ምን ይላል? ይህንን እንመልከት፡፡

ግብጽ ኢትዮጵያና አባይን ለመለያየት ወይም ከኢትዮጵያ ውጪ የሚገኙ የራስጌ ሀገሮችን ፍቅር ለማትረፍ ያላደረገችው ጥረት አልነበረም፡፡ ከእነዚህ ጥረቶች አንዱ ‘ኡንዱጉ’ የተባለውን ማህበር መመሥረት ነበር፡፡ ግብጽ ይህንን ስትመሰርት መጠሪያው ስዋህሊኛ እንዲሆን ያደረገችው ያለምክንያት አይደለም፣ በብርቱ አስባበትምር ነው፡፡ ይህ ማህበር የተመሠረተው እ.ኤ.አ በ1983 ነው፡፡ ማህበሩ የመጀመሪያውን ጉባዔ በካርቱም፣ ሁለተኛውን በዛየር ኪንሻሳ፣ ሦስተኛውን በካይሮ አካሂዷል፡፡ አራተኛውና ሌሎች ስብሰባዎችም ከዚያ በኋላ ቀጣይ ሆነዋል፡፡

እጅጉን የሚያሳዝነውና ይበልጡን የሚያስገርመው ነገር ቢኖር 85 በሙቶ የአባይ ወንዝ ምንጭ የሆነችው ኢትዮጵያ በማህበሩ ውስጥ አለመካተቷ ነበር፡፡ ግብፆች ሲያሰኛቸው ኢትዮጵያ በታዛቢነት እንድትሳተፍ ሲሻቸው የእነርሱ የእጅ ሥሪት ማህበር ሰለባ እንድትሆን ያለመታከት ይወተውታሉ። ግና ይህ ሁኔታ አዲስ ጉዳይ አይደለም – ሥልቱን እየቀያየረ የሚመጣ ወጥመድ እንጂ፡፡

ማህበሩ ቁም ለቁም ገጽታው ሲታይ ወንድማማችነትን የማጠናከር ተልዕኮ ያነገበ መስሎ ይታያል፡፡ ተጨባጭ እውነታው ግን በአባይ ላይ የሚደረጉ ማናቸውም የልማት እንቅስቃሴዎች ከግብጽ እይታ እንዳይወጡ ለማድረግ የተበጀ መቆጣጠሪያ ሥልት መሆኑን ለመገንዘብ ብዙ ጥናትና ጥልቅ ምርምር አያስፈልገውም፡፡

በኢትዮጵያ በኩል እስከ አምስተኛ ጉባዔ ድረስ አልፎ...አልፎ ድምጿን ለማሰማት ከሞመከር ባለፈ እምብዛም የረባ እንቅስቃሴ ስታደርግ አልታየም፡፡ ከዚያ ወዲህ ግን ናይል 2002 በተባለውና በኢትዮጵያ አቆጣጠር በ1993 ዓ.ም በተመሠረተው ጉባዔ ላይ ኢትዮጵያ ተሳትፋለች፡፡ ከዚህም በላይ አምስተኛውንና ስምንተኛውን የናይል ጉባዔ በማስተናገድ ወደ መጫወቻ መድረኩ ብቅ ብላ ትርጉም ያለው ተሳትፎ ማድረግ መጀመሯ ይታወቃል፡፡

“አባይን ለጋራ ብልጽግናችን በጋራ እንጠቀም” የሚለው ፍትሃዊና የሰለጠነ ሃሳብ ለዓመታት ሥፍራ ያገኘ አይመስልም፡፡ ይህን አቋሟን ከጥንት አንስቶ በጽናት ስታራምድ የኖረችውን ኢትዮጵያን ጠልፎ ለመጣል ያልተሸረበ ሴራ የለም፡፡ ኢትዮጵያ ለልማት የምታካሂዳቸው እንቅስቃሴዎች በውጥን እንዲቀሩ፣ ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ተቋማት እገዛ እንዳይሰጡ፣ የበለፀጉ ሀገሮች ድጋፍ እንዳያደርጉ የግብጽ ባለሥልጣናት በረዣዥም እጆቻቸው ሁሉን ነገር ከማድረግ አልቦዘኑም፡፡ ያሻቸውን ሲፈፅሙ ኖረዋል፡፡

"የአባይ ተፋሰስ ሀገሮች ጥቅማቸውን የሚያስጠብቅ ፍትሃዊ የውኃ ድልድል ሊኖራቸው ይገባል" በሚል ሳትታክት ትጠይቅ የነበረችውን ኢትዮጵያን ብቻዋን አስቀርቶ ለማሳጣት የግብጽ ባለሥልጣናት ብዙ ዘይደዋል፤ ነጥሎ የመምታት ሥልትንም እስከቻሉበት ድረስ ገፍተውበታል፡፡ ይህን እውነታ ትንሽ ፈታና ዘርዘር አድርገን እንመልከት፡፡ የዛሬ 27 ዓመታት ገደማ በግብጽ ባለሥልጣናት የበላይነት “ኡንዱጉ” የተሰኘ ማህበር ተመሠረተ፡፡ የአባይ ተፋሰስ አባል ሀገራትንም በአባልነት ያዘ፡፡ ከኢትዮጵያ በስተቀር፡፡

ኡንዱጉ ስዋህሊኛ ነው፡፡ ወደ አማርኛ ሲመለስ “ወንድማማችነት” እንደ ማለት ነው፡፡ ለመሆኑ ለአባይ ወንዝ በምንጭነት ከፍተኛ ድርሻ ያላትን ኢትዮጵያን ያላካተተ ስብስብ ምን ዘለቄታዊ መፍትሄ እንዲያመጣ ይጠበቅበት ይሆን? ካልሆነ ምን ለመፈየድ ታስቦ?

“ኡንጹጉ” – “ወንድማማችነት” ቆንጆ፣ ሸጋ ቃል ነው፡፡ እንደ ስሙ ከሆነ መልካም፤ ለበጎ ተግባር፣ ለጤናማ ተልዕኮ የተሰባሰቡበት ከሆነም እሰየው፡፡ ግና ማህበሩ ከመጋረጃው በስተጀርባ ድብቅ ዓላማ እንደነበረው ተደርሶበታል፡፡

የያኔዎቹ የግብጽ ከፍተኛ ባለሥልጣናት በአባይ ዙሪያ የሚካሄዱ ማናቸውንም ግንባታዎች ካይሮ ላይ ተቀምጠው ለመቆጣጠር እንዲያስችላቸው የዘየዱት መላ እንደነበር ብዙዎች አልጠፉቸውም፡፡ እስከ ዛሬ ድረስ ሁሉንም የአባይ ተፋሰስ ሀገሮች የሚያስተሳስር ወንዙንም በጋራ ለመጠቀም የሚያስችል ስምምነት ተደርጎ አያውቅም፡፡ እዚህ ላይ እ.ኤ.አ በ1929 እና በ1959 ለግብጽ ጥቅም ሲባል የተዘጋጁ ስምምነቶችን እንደ ስምምነት መውሰዱ በራሱ ህጋዊነትን ማላበስ ስለሚሆን “ወቅት የጣላቸው፣ ተቀባይነት የሌላቸው ስምምነቶች” ብሎ ማለፍ ተገቢነት ይኖረዋል፡፡

ዛሬ ያለው ነባራዊ ሁኔታ ምን ይመስላል? ዘርዘርና ፈታ አድርገን እንመልከት፡፡ የግብጽን የውኃ ተጠቃሚነት መብት በተቀበለና የተፋሰሱ ሀገሮች ተነጻጻሪ መብት ባካተተ ፍትሃዊ መርህ ላይ የተመሠረተ “አባይን ለጋራ ብልጽግና በጋራ ማልማት” የሚለው አዲሱ አስተሳሰብ ዛሬ በብዙዎቹ ዘንድ ቅቡል የሆነና ተራማጅ እሳቤ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ግብጽ በዓለም አቀፉ ህግ የወል ተጠቃሚነት መብት የሚያጎናጽፋቸው ሀገሮችን በማግለል የጋራ ሀብት የሆነውን ውኃ ሀገሪቱ በብቸኝነት ኢ. ፍትሃዊ በሆነ ሥልት ለመጠቀም እንድትሻ ያመቻቸና አቅም እንደሚፈጥርላትም ቁልጭ አድርጎ ያሳየ በመሆኑ ጭምር ነው “ወቅት ያለፈባቸውና ተቀባይነት የሌላቸው ስምምነቶች” ማለትን የመረጥኩት፡፡

የአባይ ወንዝ የተፋሰስ ሀገራቱ የጋራ ንብረት በጋራ መጠቀም ቢቻል እንዴት መልካም በሆነ፡፡ እንደተባለውም ወንድማማችነትን ይበልጡን እንደሚያጠናክረው ይታመን ነበር፡፡ እርግጥ በ21ኛ ክፍለ ዘመን ላይ እየኖርን እንደ 19ኛው ክፍለ ዘመን ማሰብ አይገባንም፡፡ ፍትሃዊ የውኃ ክፍፍል ይኑር፡፡ የውኃ ሀብቱን በጥቂት ሀገራት የበላይነትና ተጠቃሚነት የመቆጣጠር ጭፍን አስተሳሰብ አያዋጣምና ይቅር። ስልጡን አተያይ አይደለምና፡፡

ሆኖም ዛሬ ትናንት አይደለም፡፡ አሮጌው በአዲስ ተለውጧል። ያረጀ ያፈጀው በሥልጡኑ አስተሳሰብ ተተክቷል፡፡ ዛሬ ልዩነቶች በክብ ጠረጴዛ መፈታትን መርጠዋል፡፡ ለዚህም ነው የላይኞቹ ተፋሰስ ሀገራት ኢትዮጵያን ጨምሮ ኡጋንዳ፣ ኬንያ፣ ሩዋንዳና ታንዛኒያ “ሁሉም ከጋራ ንብረታቸው ፍትሃዊ የሆነ ጥቅም ያግኙ” በሚል የትብብር ስምምነቱን

የተፈራረሙት፡፡ ሁለቱ የላይኛው ተፋሰስ ሀገሮችም ስምምነቱን እንደሚፈርሙት ይጠበቃል፡፡

ይኼም ለግብጽ ባለሥልጣናት ሌላ ራስ ምታት፣ ሌላ የቤት ሥራ ሆኖ ሰንብቷል፡፡ የግብጽ ባለሥልጣናት የላይኞቹ ተፋሰስ ሀገሮች በኡጋንዳ ያከናወኑትን የትብብር ስምምነት በበጎ ዓይናቸው ሊመለከቱት አልፈቀዱምና አርፈው አልተቀመጡም፡፡ ለዚህ ማፍረሻ ይሆነናል ያሏቸውን የተንኮል ዓይነቶች ሁሉ ሲያጠነጥኑ ከርመዋል፡፡ ወደ ተግባር ለማሸጋገርም ላይ ታች ሲሉ ሰነባብተዋል - በነጥሎ የመምታት ሥልት፡፡ ያኔ የግብጽ ከፍተኛ ሹሞች የትብብር ስምምነቱን የፈረሙ ሀገራት ባለሥልጣናትን (ከኢትዮጵያ ውጪ) ተራ በተራ ወደ ካይሮ በማስጠራት በተናጠል ውይይት ሲያደርጉ መክረማቸው ተሰምቷል፡፡ ምክክሩ ለበጎ ከሆነ መልካም። ሀገራቱ የደረሱበትን የትብብር ስምምነት ለማስገልበጥ ከሆነ ግን ብዙም ስኬት የሚያስገኝ አልሆነም፡፡

የግብጽ የማግለል አካሄድ በዚህ ብቻ የተገታ አልነበረም። በአንድ ወቅትም የአባይ ተፋሰስ ሀገሮችን የሚያሳትፍ የእግር ኳስ የወዳጅነት ውድድር አሰናድታ እንደነበር ይታወሳል። ከዚህም የጥሪ መዝገብ ላይ ኢትዮጵያና ሩዋንዳ አልተካተቱም፡፡ ከቶ አባይን ከኢትዮጵያ፣ ኢትዮጵያን ከአባይ ነጥሎ ማየት ይቻል ይሆን? ደህና ይህንንም መልካም ብለን እንውሰድ፡፡ ስፖርት ለሠላም፣ ለወዳጅነት፣ ለጤንነት...አይደል የሚባለው?

በግብጽ መሪነት የዛሬ 27 ዓመታት ገደማ የተቋቋመውና ከኢትዮጵያ ውጭ ያሉ የተፋሰሱን ሀገሮች በአባልነት ያሳተፈው ማህበር ከነመጠሪያውስ “ኡንዱጉ”- “ወንድማማችነት” አይደል የሚባለው? ከበስተጀርባው ያለው ድብቅ አጀንዳ ከፋ እንጂ ስሙስ ሸጋ ነበር፡፡ ግብጽ ሙሉ ወጪውን በመሸፈን በባለቤትነት ባሰናዳችው የአባይ ተፋሰስ ሀገራት የእግር ኳስ ውድድር የጥሪ ግብዣ ያልደረሳቸው ኢትዮጵያ እና ሩዋንዳ ብቻ መሆናቸው ስለምን? ልብ ይበሉ! የግድ ግብዣ፣ የግድ ጥሪ የምንጠብቅ እንኳን አይደለንም፡፡ ያውቁናል ኩሩዎች ነን፡፡

የያኔዎቹ የግብጽ ከፍተኛ ባለሥልጣናቱ የመረጡት መስመርና የሄዱበት ጎዳና ከማህበርም ከወዳጅነት የእግር ኳስ ግጥሚያም ወጣ ያለ ጊዜ ያለፈበት ከተራ ብልጣ ብልጥነት ያልዘለለ የተበላ ዕቁብ ዓይነት ነው፡፡ ዓለም በ21ኛው ክፍለ ዘመን በጥቃቅን መደለያ ዘላቂ ሀገራዊና ብሔራዊ ጥቅሙን አሳልፎ ከማይሰጥበት ደረጃ ላይ ስለመገኘቱ ፈጥነው ያልባነኑ

ናቸው፡፡ እንዲህ ስል ምክሬን ለገስኩ፡፡ ጊዜ ያለፈባቸውን የቀን መቁጠሪያቸውን ቢገለብጡ ብዬ፡፡ ወደተነሳሁበት የአባይ ወንዝ ጉዳይ እንመለስ፡ የአባይ ውኃን አጠቃቀም በተመለከተ ኢትዮጵያ ሆነች ሌሎች አዋሳኝ ሀገሮች ሁሉን የሚያካትት ወጥ ህግ የላቸውም፡፡ ግብጽና ሱዳን የወንዙ ብቸኛ ባለቤት እንደሆኑ ሁሉ ከዚህ በፊት የነበሩት ስምምነቶችን ብቻቸውን ሲያደርጉ ቆይተዋል፡፡ ከእነርሱ ወጪ የትኛውንም የተፋሰሱ ሀገራትን ተጠቃሚ የሚያደርግ ጉዳይ በስምምነቱ ውስጥ ጨርሶ አልተካተተም፡፡

በግብጽና በሱዳን የተደረገው የ1959ኙ ስምምነት ሌሎችን የሚያካትት ሳይሆን ሙሉ በሙሉ የሁለቱን ሀገራት ጥቅም ብቻ የሚያስጠብቅ ነው፡፡ ከዓለም አቀፉ ህግና ልማዳዊ አሰራር መርሆዎች አንጻር ሲታይ ይህ ውል በሁለቱ ሀገሮች መካከል ያለውን መብትና ግዴታ ከማመላከት ባሻገር በሌሎች የተፋሰሱ ሀገሮች የተጠቃሚነት መብት ላይ የሚያስከትለው ውጤት አይኖርም፡፡ይልቁንም ዓለም አቀፉ ህግ የወል ተጠቃሚነት መብት የሚያጎናጽፋቸውን ሀገሮች በማግለል የጋራ ሀብት የሆነውን ውኃ ግብጽ በማን አለብኝነት በብቸኝነት ለመጠቀም የምታደርገውን ኢፍትሃዊና ተገቢ ያልሆነ እንቅስቃሴ ውሎቹ በጉልህ ያሳያሉ፡፡

ቀደምቶቹ የግብጽ መሪዎች ከሱዳን ጋር በርካታ ስምምነቶችን አድርገዋል፡፡ ከነዚህም መካከል እ.ኤ.አ በ1959 የዓባይ ውኃ ክፍፍል፣ እ.ኤ.አ በ1976 የመከላከያ፣ እ.ኤ.አ በ1982 ግብጻውያንን ለመጥቀም የተደረገው የጆንግሊ ካናል ቁፋሮ ስምምነቶች ዋናዎቹ ናቸው፡፡አል ኢትሃድ አልወጢኒ የተባለው ፖለቲካዊና ኃይማኖታዊ አንጃ በሱዳን ውስጥ የግብጽን ጥቅም የሚያስጠብቅ ግብጽ ዘመም ድርጅት ነው፡፡ የሁለቱ ሀገሮች ስምምነት ሲጤን አብሮ ግምት የሚሰጠው ሌላ ጉዳይም አለ፡፡ ሰፊ ጉዳዮችን የያዘ ነው፡፡

ያም ሆኖ ግብጽ በተለይ በአባይ ውኃ ላይ የመሠረተችውን አግላይ የይገባኛል ይዞታ ጠብቃ ለመቆየት ስትል በኢትዮጵያ ላይ የምታደርገው ግልጽና ስውር ፖለቲካዊና ዴፕሎማሲያዊ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅምና ደህንነት ላይ ያስከተለው ችግር ከምንጩ ሊቀረፍ ይገባዋል፡፡ እዚህ ላይ ሁሉንም የተፋሰሱን ሀገሮች መብት የሚያስተናግድ ፍትሃዊ የውኃ ድልድል ቀመር በማራመድ በኢትዮጵያ በኩል የሚታየው ጥረት ዛሬ ላይ አድናቆት ሊቸረው የሚገባ፣ ብልህና አስተዋይ ርምጃ መሆኑ ግልጽ እየሆነ መጥቷል፡፡ እናም ጊዜ ያለፈባቸው ስምምነቶችን ከተቀበሩበት ቦታ አቧራቸውን አራግፎ የመጠቀም ፖለቲካ አዋጭነቱ በምድረ በዳ ላይ እህል ዘርቶ ምርት የመጠበቅ ያህል ነው፡፡